# የአፍሪካ አፈ ጉባኤ

**ዮናስ 8/28/12**

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለአፍሪካ ቀንድ ሰላም መስፈንና ለአፍሪካ ልማት የተጫወቱት ሚና መቼም ቢሆን ከመላው አፍሪካውያን ልብ የማይወጣ ነው፡፡ ለዚህም ነው የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መታመም ከተደመጠበት እለት አንስቶ አህጉሪቱ የሃዘን  ማቅ ለብሳ የሰነበተችው፡፡

”መላው የአፍሪካ ህዝብ የማይዘነጋቸው ቆራጥ መሪ ናቸው” የጠቅላይ ሚኒስትሩን ህልፈተ ህይወት ተከትሎ የደቡብ ሱዳኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሰጡት አስተያየት ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩን መላው የአፍሪካ ህዝብ የማይዘነጋቸው ለልማት፣ ለሰላም ለዴሞክራሲና ለመልካም አስተዳደር በአፍሪካ እውን መሆን፤ አፍሪካ በአለም አቀፍ መድረክ ያላትን ዝቅተኛ ዕይታና ምልከታ ከፍ ወዳለ ደረጃ በማሸጋገርና የአለማችን አንዱ ሊያውም ወሳኝ ክፍለ አህጉር መሆኗን ተሟግተው በተጨባጭ ያረጋገጡና ያሳመኑ በመሆናቸውና አፍሪካ ዛሬ ለደረሰችበት ደረጃ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ድርሻ ከሁሉም የአፍሪካ መሪዎች በእጅጉ የላቀ በመሆኑ ነው፡፡

በተለይም ደግሞ የግጭት ቀጣና በሆነው የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ከልጅነት እስከ እውቀት መፍትሄ ጠፍቶላቸው  ሲያወዛግቡ የከረሙ ድንበሮችንና ይገባኛል ባዮችን በማደራደርና ወደሰላም ተመልሰው ችግሮቻቸውን በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ያደረጉት ጥረትና ያስገኙት ውጤት ደግሞ ከሁሉም ይልቃል፡፡

በዚህ ረገድ ደቡብ ሱዳናውያን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያላቸው አድናቆትና ስሜት ከኛም ከኢትዮጵያውያኑ የተካከለ ነው፡፡ የደቡብ ሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ኒሃል የደቡብ ሱዳን መንግስትና ህዝብ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት እጅግ ማዘናቸውን ገልጸው ”ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለደቡብ ሱዳን ሰላም መስፈን እና ለነፃነቷ መከበር ያበረከቱት አስተዋጽኦ የማይዘነጋ ነው” ማለታቸውና በተለይም የደቡብ ሱዳን መንግስት በተለየ መልኩ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞት የተሰማውን ሃዘን ለመግለጽ በመላ አገሪቱ የሶስት ቀናት ብሄራዊ ሃዘን ማወጁ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአፍሪካ አፈጉባዔ ስለመሆናቸው ዓቢይ ማሳያና ማረጋገጫ ነው፡፡

የኬንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ህልፈት ተከትሎ የሰጡት አስተያየትም እንዲሁ ከደቡብ ሱዳኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ያልተለየና የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን የአፍሪካ አፈጉባኤነት ያረጋገጠ ነው፡፡ በተለይ በሶማሊያና በቀጠናው ሰላም እንዲሰፍን ኢትዮጵያና ኬኒያ በጋራ ያከናወኗቸው ተግባራትና አፈጻጸም ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የነበራቸውን ሚና ስላሳሰባቸው ይመስላልበሶማሊያና በቀጣናው ሰላም እንዲሰፍን ሁለቱ አገሮች እያከናወኑ ያለው

ስራ በቀጣይ ጊዜያትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል መንግስታቸው ፍላጎት ያለው መሆኑን በመናገር ነው ለመላው ኢትዮጵያውያንና የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቤተሰቦች መጽናናትን በመመኘት ሃዘናቸውን የገለጹት፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ለእኛ ለኢትዮጵያውያን በተለይ በታሪክ እንደህዝብና ኢትዮጵያዊ ብዙ ነገሮችን ተነፍገን የኖርንባቸውን ዓመታት እንድንዘነጋና በአዲስ መንፈስ እንድንጓዝ ያደረጉ መሪ ናቸው፣ መለስ ለኛ ለኢትዮጵያውያን ልማት ናቸው፣ መለስን ስናነሳ ሰላምን እናስታውሳለን፣ መለስን ስናስታውስ ዴሞክራሲን እናስባለን፣ በተለይም ለወጣቶችና ሴቶች እነዲሁም አርሶ አደሮች መለስ የተለዩ ናቸው፣ ትርጉማቸውም ሰፊና ዘመን ተሻጋሪ ነው፡፡

ለመላው አፍሪካውያን ደግሞ ድምጽ ናቸው፡፡ ስለሆነም መላው አውሮፓውያንና አሜሪካውያን የአፍሪካ አፈጉባዔ ስለመሆናቸው ያረጋግጣሉ፡፡ ሞታቸውን ተከትሎ የተሰጡ አንድ ሶስት አስተያየቶችን እንመልከት፦

"ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር የተገናኘሁት በቡድን ስምንት አገሮች የመሪዎች ስብሰባ ላይ ነበር፡፡ ሁሌም ቢሆን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ከድህነት ለማላቀቅ ለሚያስችለው የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ለሰጡት ልዩ ትኩረት ከፍተኛ አድናቆት አለኝ፡፡ በተጨማሪም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ለአፍሪካ ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ለአፍሪካ ህብረትና ድምፅ በአለም አደባባይ መሰማት ላበረከቱት አስተዋጽኦ ባለእዳነት ይሰማኛል፡፡" ይህን ያሉት የአሜሪካው ፕሬዜዳንት ባራክ ኦባማ ናቸው፡፡

ወደር በሌለው የመሪነት ብቃታቸው ምን ጊዜም እንደማይዘነጓቸው በመግለጽ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሞት በተመለከተ አስተያየት የሰጡት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሃፊ ባንኪ - ሙን የጠቅላይ ሚኒስትሩን የአፍሪካ አፈጉባኤነት ያረጋገጡት "አፍሪካን በተመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በአህጉር ደረጃና ከአህጉር ባሻገር ያራመዷቸው አቋሞች ፍፁም የተለየ ስፍራ እንዲሰጣቸው የሚያደርጉ ናቸው፡፡" በማለት ነው፡፡

የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ስለነበራቸው ተሰሚነትና ወሳኝነት በመናገር ነው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን የዘከሩት፡፡

ወሳኝነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ጉዳዮችና አጀንዳዎች ዙሪያ አሳማኝና ተቀባይነት ያላቸውን ሃሳቦች በማቅረብ በሚል የአመራር ብቃትና ችሎታቸውን ያሳዩ ታላቅ መሪ እንደነበሩ ያወሱት ዴቪድ ካሜሮን በተለይም የሱዳን እና የሶማሊያ ችግሮች እንዲፈቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የሰጡት አመራርና ራዕያቸው የሚደነቅ ነው በማለትም አሞካሽተዋቸዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በአለም አቀፍ የፖለቲካ መድረክ በእጅጉ ተደማጭነት ያላቸው "የአፍሪካ ቃል አቀባይ" ሲሉ ያወደሷቸው የአለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ማኔጂንግ ዳይሬክተር ክርስቲን ሊግሬድ ኢትዮጵያ የተቀዳጀቻቸው ድሎች እና ያስመዘገበቻቸው ውጤቶች በርካቶች መሆናቸውን በማስታወስ ኢኮኖሚያዊ እድገት በማፋጠን እና ድህነትን በመቀነስ ረገድ ለታየው እምርታ የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የአመራር ብቃት በዋነኝነት የሚጠቀስ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊን ህልፈተ ህይወት ተከትሎ የተለያዩ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሃኖች ያስተላለፏቸውን ዘገባዎችም ስንመለከት የምናረጋግጠው ይህንኑ የመለስን የአፍሪካ አፈጉባዔነት ነው፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር መለስን ሞት "የአፍሪካ ህዳሴ ሞት" ሲል በድረ ገጽ ያሰፈረው ኤዥያ ታይምስ የአፍሪካ የቤት ስራና ተስፋ ያረፈው  በአቶ መለስ ትከሻ ላይ እንደነበር የሚገልጸው ኤዥያ ታይምስ የደርግ ስርዓትን በመገርሰስ ዴሞክራሲን በማስፈንና ፖለቲካዊ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ በማድረግ ለውጥ ያመጡ ጠንካራ መሪ እንደነበሩ  በመግለጽ ነው ጽሁፉን ያሰፈረው፡፡ በዚህ ያላበቃው ኤዢያ ታይምስ የቀድሞውን የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ቢልክሊንተን "አፍሪካን መለወጥ የሚችለው አዲሱ የመሪዎች ትውልድ" የሚል ንግግር በማስታወስ እነዚህ የትውልዱ አፍሪካውያን መሪዎች የአፍሪካን ህዳሴ ለማረጋገጥ የሚችሉ እነደሆነ ቢል ክሊንተን ቀድሞውንም ቢሆን መተንበያቸውን ገልጿል፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የአፍሪካ አፈጉባዔነት የተረጋገጠበትን ሌላኛ ዘገባ የተመለከትነው ከፈረንሳይ ዜና አገልግሎት ኤ.ኤፍ.ፒ ነው፡፡ ዘገባው እንዳመለከተው የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ሞት ለምስራቅ አፍሪካ አካባቢ አገሮች ትልቅ ኪሳራ ነው፡፡ "የአካባቢው ጠንካራ መሪ" ሲል ያወዳሳቸው ኤ.ኤፍ.ፒ በአካባቢው ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን ያደረጉትንም ትግል አስታውሷል፡፡

የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ "ድህነትን ከአገራቸው ለማጥፋት የማይተኙ ነበሩ" ማለታቸውን የገለጸው ኤ ኤፍ ፒ የደርግ ስርዓት መውደቅን ተከትሎ አገሪቱን ላለፉት 21 ዓመታት መምራት የቻሉና በአገሪቱ አስገራሚ አኮኖሚያዊ እድገት በማስመዝገብ የሚታይ አሻራቸውን ማሳረፋቸውን እና በአካባቢው ሰላም እንዲሰፍን በአደራዳሪነት ቁልፍ ሚና ተጫውተው እንዳለፉ ዘገባው መስክሯል፡፡

ቢቢሲ፣ አልጀዚራ፣ ሮይተርስ፣ አሶሽየትድ ፕሬስ፣ በተመሳሳይ አቶ መለስ በኢትዮጵያ፣ ለምስራቅ አፍሪካ፣ ለመላ አፍሪካ፣ እንዲሁም ለዓለም ማህበረሰብ እውቀታቸውን እና ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ ማበርከታቸውን በመግለጽ ታላቅ መሪ እንደነበሩና የአፍካ አፈጉባኤ ስለመሆናችው አረጋግጠዋል፡፡

የኡጋንዳው ፕሬዝዳንት ዩዌሪ ካጉታ ሙሴቬኒ፣ የቀድሞው የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ዶክተር ዣን ፒንግ፣ የኢጋድ ዋና ፀሃፊ ኢንጅነር ማህቡብ ማለሞ፣ አዲስ አበባ የሚገኙት የቻይና እና የቬንዙዌላ ኤምባሲዎች በጠቅላይ ሚኒስትሩ ዕረፍት የተሰማቸውን ሃዘን በመግለጽ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብና ለጠቅላይ ሚኒስትር ቤተሰቦች መጽናናትን የተመኙት ለአፍሪካ እንደሚጎልባት በማመን ነው፡፡

የአውሮፓ ህብረት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት ሚስተር ኸርማን ሮምፑይ እና የህብረቱ ኮሚሽን ፕሬዝዳንት ጆሴ ማኑዌል ባሮሦ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ህልፈተ ህይወት የተሰማቸውን ሃዘን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ መልማትና አንድነት፣ሰላምና መረጋጋት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ መሪ እንደነበሩ በማስታወስ ነው፡፡

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአሜሪካ ቋሚ ተወካይ አምባሳደር ሱዛን ኢ.ራይስ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በአፍሪካ ሰላምና ደህንነት እንዲሰፍን ያደረጓቸው እጅግ በርካታ አስተዋጽኦዎች ትልቅ ዋጋ የሚሰጣቸው መሆኑን ገልጸው ረዥሙ የሱዳን የእርስ በእርስ ጦርነት እንዲያበቃና በአፍሪካ አዲሲቷ አገር ደቡብ ሱዳን እንደትመሰረት ያስቻለው ሁሉን አቀፍ የሰላም ስምምነት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲተገበር ያደረጉት ወሳኝ ድጋፍ፣ በተለይ በሶማሊያ አሸባሪነትንና ጽንፈኝነትን በጽናት መዋጋታቸው እንዲሁም በላይቤሪያና በቡሪንዲ የነበሩ ግጭቶችን ለማስቆም ያደረጉት ጥረትም የተሳካ እንደነበር በማውሳት ባጠቃላይ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የአፍሪካ አፈ ጉባዔ እንደነበሩና ለአፍሪካ ህዳሴ እስከ መጨረሻዋ ቀሪ “ አንድ ግራም” ጉልበታቸው ድረስ መልፋታቸውን ሁሉም ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፡፡